በመስከረም ፳፻፰ ዓ.ም  ከዲያቆን ዳንኤል ክብረት የቀረበና ለዓለም የተሰራጨ መልዕክት

**የዘመናችን አጥማቂ ነን ባዮች፡- የሐሳዊው መሲሕ መንገድ ጠራጊዎች**

**ክፍል አንድ**

በዚህ ዘመን በተደጋጋሚ ከሚነሡ መንፈሳውያን ጥቄዎች መካከል አንዱ የጥምቀትና አጥማቂዎች ጉዳይ ነው፡፡ ጥምቀት(የክርስትና ጥምቀትን አይመለከትም) በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ምእመናን ፈውሰ ሥጋ ፈውሰ ነፍስ እንዲያገኙባቸው ከእግዚአብሔር ከተሰጡ ጸጋዎች አንዱ ነው፡፡(2ኛ ነገሥት 5፤ ዮሐ. 5፣ ዮሐ. 9)፡፡ በቤተ ክርስቲያን ታሪክም ውስጥ በልዩ ልዩ ገድላተ ቅዱሳን ላይ እንደምናነበው በጠበል ሕዝቡን ሲፈውስ ኖሯል፡፡ ሕዝብ ፈውስ የሚያገኝባቸው እንደ ሰሊሆምና እንደ ቤተ ሳይዳ የታወቁ የቃል ኪዳን ቦታዎችም ነበሩ፡፡

አሁን በያዝነው ዘመን አያሌ ‹አጥማቂ> የሚባሉ ሰዎች ተነሥተዋል፡፡ ክብራቸውን የሚገልጥ ማስታወቂያ ያስነግራሉ፣ መቁጠሪያ ይሸጣሉ፣ ቅባት ይቀባሉ፣ አዳራሽ ከፍተው ወይም ሕዝብ በሜዳ ሰብስበው እንፈውሳለን ይላሉ፤ ሰይጣን ተናገረ የሚባለውን በካሴት ቀድተው ይሸጣሉ፡፡ ከዚህ ቀጥዬ በማቀርባቸው አሥር ምክንያቶች እነዚህን ሐሳውያን መቀበል የለብንም ብዬ አምናለሁ፡፡

1. በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ገዳማዊ ሕይወት፣ ክህነታዊ ሕይወት፣ የጸሎት ሕይወት ወይም ሌላ አንዳች ተጋድሎ ሳይኖረው ማጥመቅ ብቻ ሥራው የነበረ ክርስቲያን የለም፡፡ ሀብተ ፈውስ የተሰጣቸው አባቶችና እናቶች የሌላው መንፈሳዊ ሕይወታቸው ውጤት ወይም ነጸብራቅ ነበር እንጂ ሥራቸው እየዞሩ ማጥመቅ አልነበረም፡፡ የሐዋርያት ሥራን ብናነብ ሐዋርያት ለወንጌል አገልግሎት ሲሠማሩ በአንድ በኩል አሕዛብን ወደ ክርስቶስ ለመጥራት በሌላ በኩል የአንደበት ትምህርታቸውን በእጃቸው ተአምር ለማጽናት  ተአምራትን ያደርጉ ነበር እንጂ በአንድ ከተማ ውስጥ ሲያጠምቁ ውለው ያደሩበት፣ ወይም ከወንጌል አገልግሎት ተለይተው አጥማቂ ብቻ የሆኑበት፣ ወይም ደግሞ በዚህ ቦታ ፈውስ እንሰጣለንና ተሰብሰቡ ብለው ያስነገሩበት አንድም ማስረጃ የለም፡፡ በገድለ ቅዱሳንም ቅዱሳን ጸጋ እግዚአብሔር ሲያድርባቸው፣ ሥጋቸውንና ሰይጣንን ድል ሲነሡ፣ በክርስትናቸው ሲበስሉ ተአምራት ይከተሏቸዋል እንጂ እንዲሁ ማጥመቅና መፈወስ ብቻ ሕይወቱ የነበረ ቅዱስ የለም፡፡ ሰው ያለ ተጋድሎ እንዴት ጸጋ ያገኛል፡፡ በአሁኑ ዘመን ግን ከተራ ሰዎች የተለየ መንፈሳዊ ሕይወት የሌላቸው ሁሉ እየተነሡ አጥማቂ ሊሆኑ የቻሉበት አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡

2. በገድለ ቅዱሳን ውስጥ ቅዱሳን በገዳማዊ ሕይወት፣ በሰማዕትነት፣ በክህነታዊ አገልግሎት ሲሠማሩ እግዚአብሔር ምእመናንን ለመጥቀም ወይም ክብረ ቅዱሳንን ለመግለጥ በእነርሱ ላይ ተአምራትን ያደርጋል፡፡ እነርሱ ግን ይህ ክብር እንዳይገለጥባቸው ሲሸሹ፣ እኔ አላደረግኩም ሲሉ ወይም ስለራሳቸው ደካማነት ሲነገሩ እናያለን እንጂ ‹ኑ እንፈውሳችኋላን› ብለው ዐዋጅ ሲናገሩ አይተንም፣ አንብበንም አናውቅም፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም ወጥተው ወደ ሐይቅ

እስጢፋኖስ  ገዳም የሄዱበት ዋናው ምክንያት በገዳሙ እያሉ በፈወሱት አንድ በሽተኛ ምክንያት ስማቸው ከፍ በማለቱ፣ ብዙ ሰዎችም በመሰብሰባቸው የተነሣ ነው፡፡ ታላቁ አባት መቃርዮስ ገዳሙን ትቶ ወደ አንዲት መንደር መጥቶ የኖረው በገዳሙ ክብሩ በመገለጡና ተአምራቱ በመታየታቸው ከከንቱ ውዳሴ ለማምለጥ ነበር፡፡ ስምዖን ጫማ ሰፊው አካባቢውን ትቶ የጠፋው ተአምር አድራጊነቱ በመታወቁ ምክንያት ነበር፡፡ አሁን ግን ከዚህ በተቃራኒው ሰዎች እናጠምቃለን፣እንፈውሳለን ብለው ማስታወቂያ የሚያስነግሩበት፣ ካሴት የሚሸጡበት፣ ፖስተር የሚሰቅሉበት ዘመን ነው፡፡

3.	ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ ማን እንደሆነ፣ ድንግል ማርያም ማን እንደሆነች፣ ቅዱሳን መላእክት ማን እንደሆኑ ሌሎቹም ቅዱሳን ማን እንደሆኑ ጠንቅቃ ታውቃለች፡፡ የእግዚአብሔርን ክብር ለሰዎች ሰጥታ አታውቅም፡፡ ቅዱሳንን ከፈጣሪ አስበልጣ አታወቅም፡፡ የቅዱሳን መገኛና መሠረት በባሕርዩ ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር መሆኑን ታምናለች፣ታስተምርማለች፡፡ ለእግዚአብሔር የማይቻል ለቅዱሳን ይቻላል፣ በእግዚአብሔር የማይሠራ በቅዱሳን ይሠራል ብላ አታምንም፣ አታስተምርም፡፡ በዘመኑ አጥማቂዎች ዘንድ የምናየው ግን ከዚህ በተቃራኒው ነው፡፡ በክርስቶስ ስም የማይወጣው ሰይጣን የቅዱስ ሚካኤልን ስም ሲጠሩበት ይወጣል፡፡ በክርስቶስ ስም የሚያሾፍ ሰይጣን የድንግል ማርያምን ስም ሲጠሩበት ተቃጠልኩ ይላል፡፡  ይኼ ፈጽሞ ክህደት ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያንም ትምህርት አይደለም፡፡ ‹‹በስመ ሥላሴ እቀጠቅጥ ከይሴ›› ብላ ያስተማረች ቤተ ክርስቲያን ላይ ‹‹በክርስቶስ ስም አንወጣም፣ በማርያም ስም ግን እንወጣለን›› እያለ አጋንንት ወጣ የሚል ትምህርት ማስፋፋት ክህደት ነው፡፡

4.	መቁጠሪያ በቤተ ክርስቲያናችን ለጸሎት መቀስቀሻና ማስታኮቻ የሚውል ነው፡፡ ምእመናን እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ፣ በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ፣ ኪርኤ ኤላይሶን የተባሉትን የምሕላ ጸሎቶች በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የተመደበላቸውን ቁጥር ሳይስቱ እንዲጸልዩ የተሠራ ሥርዓት ነው፡፡ በጸሎት ጊዜ ዝንጋኤ እንዳይገጥማቸው ኅሊናቸውን ለመሰብሰብም ይረዳል፡፡ አንድ ቅዱስ ለብዙ ዘመን የጸለየበት መቁጠሪያ፣ የተደገፈበት መቋሚያ፣ የቆመበት ምድር፣ የለበሰው ልብስ፣ የተጠቀመበት መጽሐፍ ተአምራት ቢያደርግ አይገርምም፡፡ ቅዱሳን የነፍሳቸው ቅድስና ለሥጋቸው፣ የሥጋቸውም ለልብሳቸው፣ የልብሳቸው ለጥላቸው ተርፎ አይተን እናውቃለንና(የሐዋ. 5፣12-17፤ 19፣ 11-12)ከዚህ ውጭ ግን የሚሸጥ መቁጠሪያ ሰይጣን የሚያስወጣበት፣ ሰው ራሱን በመቁጠሪያ ስለደበደበ ከዲያብሎስ እሥራት የሚፈታበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ ሰይጣን በጾምና በጸሎት እንጂ በመቁጠሪያ ድብደባ አይለቅም(ማቴ.17፣21)፡፡ ያ መቁጠሪያ ተአምር የሚሠራ ቢሆን እንኳን አንድ ቅዱስ የተጋደለበት፣ ከዚያ ቅዱስም በረከት ያተረፈ መሆን አለበት፡፡ ልክ የቅዱስ ጳውሎስ የጨርቁ እራፊ ይፈውስ እንደነበረው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ታሪክም የትኛውም አባት መቁጠሪያ ሲያድልና በመቁጠሪያ ሰይጣን ታወጣላችሁ ብሎ ሲያስተምር አልታየም፡፡

5.	ጌታችን በሺዎች የሚቆጠር ሕዝብ አስተምሯል፡፡ በጌንሳሬጥ ምድር አምስት ሺ(ማቴ 1413-21)፣ በገሊላ ባሕር አጠገብ አራት ሺ(ማቴ 15፣32-39)፣ ይህ ሁሉ ሕዝብ የቃሉን ትምህርት የእጁን ተአምራት አይቶ ይኼድ ነበር እንጂ ሰይጣን አድሮበት በአንድ ጊዜ የጅምላ ጩኸት ሲጮህ ታይቶ አይታወቅም፡፡ የተወሰኑ ሰዎች ግን እየቀረቡ ፈውሰ ሥጋ ፈውሰ ነፍስ አግኝተዋል፡፡ በዚህ ጊዜም ቢሆን

መድኃኒት ያደረገብሽ፣ ድግምት ያስደገመብህ፣ መተት ያስመተተብህ እገሌ ነው የሚል ሰይጣን አልተሰማም፡፡ ዛሬ ግን በአንድ ቦታ ለጥምቀት የሚሰበሰቡ ሰዎች አብዛኛዎቹ ይጮኻሉ፡፡ ሁሉም በሰይጣን ተይዘዋል ይባላሉ፣ ሁሉም ድግምት፣ መተት፣ መድኃኒት፣ ጥንቆላ እንደተደረገባቸው ይነገራቸዋል፡፡ ሰይጣንን አምነው ከባሎቻቸው፣ ከሚስቶቻቸው፣ ከእኅት ወንድሞቻቸው፣ ከጎረቤቶቻች፣ ከሥራ ባልደረቦቻቸው ይጣላሉ፡፡ ከባቴ አበሳነትን ፈጽሞ የረሳ፣ ከፍቅር ይልቅ ጠላትነትን ለማስፈን የመጣ፣ ሰዎች እግዚአብሔርን አምነው ከመፋቀር ይልቅ ሰይጣንን አምነው እንዲጣሉ የሚያደርግ የሰይጣን አሠራር ነው፡፡ ለመሆኑ ይህንን ሁሉ ሕዝብ ሰይጣን ሲቆጣጠረው ክርስቶስ የለምን? የተጠመቅነው የልጅነት ጥምቀት፣ የቆረብነውስ ቁርባን አይሠራምን? ገና ወደ ክርስትና ያልመጡ የገሊላ ክርስቲያኖች እንኳን በጩኸት አልተደበላለቁም እንኳን እኛ በክርስቶስ ክርስቲያን በወልድ ውሉድ የተባልነው፡፡ ይህ አሠራር የክርስቶስን ነገረ ድኅነት የሚፃረርና ከማዳን ሥራውም የወጣ ነው፡፡ ከክርስቶስ ክብርና ኃይል ይልቅ የሰይጣንን ኃይል ለማሳየት የሚሠራም ነው፡፡

6. ለመሆኑ ስመ እግዚአብሔርን የሚጠራ ሁሉ ትክክለኛ ነውን? አንዳንድ ምእመናን እንዲህ ይላሉ ‹እግዚአብሔርን ይጠራሉ፣ እመቤታችንንም ያከብራሉ››፡፡ ልክ ነው ሰይጣን ለአመሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል ይባላል፡፡ ሰይጣን ምንም እንኳ የሐሰት አባቷ ቢሆንም (ዮሐ. 8፤44) ሙሉ ውሸት ግን አይናገርም፡፡ በከፊል እንጂ፡፡ ሔዋንን ‹ንግሥተ ሰማይ ወምድር› ሲላት ከፍሎ ነው የዋሻት፡፡ ንግሥተ ምድር ናት፤ ንግሥተ ሰማይ ግን አልነበረቺም፡፡ በወንጌል ውስጥ አጋንንት ስመ እግዚአብሔርን ጠርተው ያውቃሉ፡፡ ሰይጣን ጌታን ሲፈትነው ከቅዱሳት መጻሕፍት ጠቅሶ ነው(ማቴ 4)፤ ጌታችን በጌርጌሴኖን ያገኛቸው አጋንንት ያደሩባቸው ሰዎች ‹የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ› ብለው ነበር የተናገሩት፡፡ ንግግራቸው ልክ ነው፡፡ እነርሱ ግን አጋንንት ናቸው፡፡ ጌታም አስወጣቸው እንጂ ማን ድግምት እንዳደረገባቸው አላናዘዛቸውም፡፡ በሌላ ቦታም በምኵራብ ሲያስተምር አንድ ሰይጣን ያደረበትን ሰው አመጡለት፡፡ ሰይጣኑም ‹‹የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ‹ ብሎ ነበር የጠራው፡፡ ጌታ ግን ‹ዝም ብለህ ወጣ› አለው እንጂ መድኃኒት ማን እንዳደረገ ተናገር አላለውም(ማር. 1፤21-28)፡፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ ስላለውም ሰይጣንነቱን አልቀየረውም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስተምር ፊልጵስዩስ የተባለ ከተማ ደረሰ፡፡ በዚያም አንዲት በርኩስ መንፈስ የተያዘች ሴት እየተከተለቺው ‹‹የመዳንን መንገድ የሚነግሯችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው›› አለች፡፡ ሴትዮዋ የተናገረቺው ምንም ስሕተት የለውም፡፡ እነ ቅዱስ ጳውሎስ የመዳንን መንገድ ያስተምራሉ፡፡ የልዑል አምላክ ባሪያዎችም ናቸው፡፡ ይህ ትክክል ስለሆነ ግን ቅዱስ ጳውሎስ ዝም አላለም፡፡ መንፈሱን አስወጣው እንጂ(የሐዋ.16፤16-18)፡፡ እነዚህ ሁሉ የሚነግሩን አንድ ሰው ስመ እግዚአብሔርን ወይም ስመ ቅዱሳንን ስለጠራ ብቻ ትክክል መሆኑን እንደማያሳይ ነው፡፡ እርስ በርሱ የማይጣረስ ርቱዕ የሆነ እምነትም ያስፈልገዋል፡፡ ርቱዕ የሆነ ሕይወትም ያሻዋል፡፡ በክርስትና አንድ ሰው መንገዱ ትክክል ሳይሆን ውጤቱ ትክክል ሊሆን አይችልም፡፡ ያለ ትክክለኛ እምነት፣ ያለ ትክክለኛም መንፈሳዊ ሕይወት ትክክለኛ ተአምራት ሊኖረው አይችልም፡፡ በሲኦል በኩል ወደ ገነት ሊገባ አይችልምና፡፡

7. ተአምራት ማድረግ ብቻውን የቅድስና ማሳያ አይደለም፡፡ ተአምራት ከመንፈሳዊ ሕይወት ብቃት ሲመነጩ እንጂ፡፡ ተአምር ከመንፈሳዊ ሕይወት ብቃት የመጣ ሲሆን ‹ስም በመንግሥተ ሰማያት በመጻፉ

እንጂ በድንቅ ነገር ማንም ደስ አይለውም››(ሉቃ. 10፣ 17-20)፡፡ ተአምራትን ሲከተሉ መኖርም የአሕዛብነት ምልክት እንጂ የክርስትና ምልክት አይደለም(ማቴ. 12፣ 39)፡፡ የክርስትና ዋና መሠረቱ ክርስቲያናዊ ትምህርት፣ ክርስቲያናዊ እምነትና ክርስቲያናዊ ሕይወት ናቸው፡፡ አንዳንዶች በማርቆስ ወንጌል መጨረሻ ላይ(ማር 16) ‹‹ያመኑት እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል›› የሚለውን ይጠቅሳሉ፡፡ እዚህ ላይ ያመኑት የተባሉት ‹የበቁት› ማለት ነው፡፡ ያማ ባይሆን ኖሮ ሁላችንም ተአምር ስናደርግ መኖራችን ነበር፡፡ አምነናልና፡፡ ደግሞም ያመኑት የሚለው ለሁላችንም ይሠራል ካልን እስኪ መርዝ ጠጥተን ምንም ሳንሆን ፣እባብም ጨብጠን ስንተርፍ እንየው፡፡ ይህ ሁሉ ግን በእመነት ለበሰሉ የሚቻል ነው፡፡ በሐዋርያት ሥራም በሐዋርያት እጅ ያመኑት ሁሉ ተአምር ሲሠሩ አናይም፡፡ በሐዋርያት ሥራ ድንቅ ሲሠሩ የምናያቸው ክርስቲያኖችም በጸሎት የተጉ፣ በሐዋርያነት አገልግሎት ሰማዕትነት የከፈሉ፣ በገድል የተቀጠቀጡ ናቸው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ራሱ ሕይወቱ በተአምራት ከመገለጡ በፊት በሱባኤ የተወሰነ ነበረ(የሐዋ. 13፣ 1-3) የዛሬ አጥማቂዎች ግን ማጥመቅ ፕሮፌሽናቸው እንጂ የመንፈሳዊ ሕይወታቸው መገለጫ አይደለም፡፡ እንዲህ ባለው ገዳም በገድል የኖሩ፣ እንዲህ ያለ መሥዋዕትነት ለክርስትና የከፈሉ ወይም ለምእመናን አርአያ የሚሆን እንዲህ ያለ መንፈሳዊ ሕይወት የነበራቸው ናቸው ተብሎ የማይመሰከርላቸው ራሳቸውን በራሳቸው የሾሙ ናቸው፡፡

8. የሰይጣን ምትሐትም አለ፡፡ የሙሴ ጸጋና ሕይወት ድል እንዲሆኑ ባያደርጋቸው ኖሮ የፈርዖን ጠንቋዮች ብዙ አስደናቂ ነገር ሠርተው ነበር(ዘጸ. 7፣8- 13)፡፡ በዘመነ ሳዖል የነበረቺው ሟርተኛም የሙታንን መንፈሶች ትጠራ ነበር(1ኛ ነገሥት. 28፣ 8-24)፡፡ አይሁድም አጋንንትን ያወጡ ነበር(የሐዋ. 19፣13)፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም የሐሳዊ መሲሕን አመጣጥ ሲያስተምረን ‹‹የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች፣ በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመጽም ማታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው›› ይላል (1ኛ ተሰ. 2፣9)፡፡ ይህም ከመንፈሳዊ ብቃት የማይመጣ ተአምር፣ ድንቅና ምልክት ምንጩ ከሰይጣን እንደሆነ ይጠቁመናል፡፡ ዛሬ በእነዚህ ይህንን ያህል የምንታለል ከሆነ ነገ ሐሳዊ መሲሕ ከዚህ የሚበልጡ አስደናቂ ተአምራትን ሲያደርግ ጨልጠን ገርኝተን መከተላችን የማይቀር ነው፡፡ ‹‹የተመረጡትን እንኳን እስኪያስት ድረስ›› ተብሏልና፡፡

9. ምሥጢረ ቀንዲል መሠረቱን መጽሐፍ ቅዱስ ያደረገ(ያዕቆብ. 5፣13) ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ነው፡፡ የሚፈጸመው በካህናት ሲሆን የራሱ የሆነ የጸሎትና የመቀባት ሥርዓት አለው፡፡ ለዚህም መጽሐፈ ምሥጢረ ቀንዲልን ማንበብ ይጠቅማል፡፡ አሁን የምናየው ግን በጀሪካል ቅባት ይዞ ማከፋፈል፣ ምእመናን ከአጥማቂዎች ‹ቅብዐ ቅዱስ› ወስደው እንዲጠጡና እንዲቀቡ ማድረግ፣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያልነበረ፣ በምሥጢረ ቀንዲል ያልተፈቀደና በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ የሌለ ነው፡፡ አንዳንድ አጥማቂዎችም ‹‹ከኢየሩሳሌም የመጣ ነው›› ይላሉ፡፡ ከኢየሩሳሌም የሚመጣ የተለየ ቅባት የለም፡፡ አንድን ቅባት ቅዱስ የሚያደርገው ጸሎቱና ሥርዓቱ እንጂ የተሠራበት ከተማ አይደለም፡፡ ኢየሩሳሌም ውስጥ ግሪክ ኦርቶዶክሶች፣ ካቶሊኮች፣ የይሖዋ ምስክሮች፣ ፕሮቴስታንቶች፣ ሌሎችም አሉ፡፡ ከኢየሩሳሌም የመጣ ማለት ከየት የመጣ ነው? ምእመናን ለኢየሩሳሌም በጎ ኅሊና ስላላቸው ‹‹ከኢየሩሳሌም ተባርኮ የመጣ ›› ይባላል፡፡ ማን ባረከው? ብሎ የሚጠይቅ የለም፡፡

10. ከአክባሪው ይልቅ ከባሪው፣ከሰጭው ይልቅ ተቀባዩ፣ከጌታው ይልቅ አገልጋዩ የሚከብርበት ሥራ የእግዚአብሔር አይደለም፡፡ መንፈሳዊ አገልግሎት ዓላማው እግዚአብሔርን ማክበር፣ አሕዛብም እግዚአብሔርን እንዲያውቁ ማድረግ፣ ከመንገድ ጠራጊውም ይልቅ መንገዱን እንዲያገኙት ማስቻል ነው፡፡ አሁን የምናያቸው ‹አጥማቂዎች› እና ‹ተአምራት› አድራጊዎች ግን ራሳቸውን የሚያከብሩ፣ እግዚአብሔርን የሚሸፍኑ፣ ሕዝቡ ቅዳሴና ትምህርት እየተወ እነርሱን በየሜዳው እንዲከተል የሚደርጉ፣ ሕዝቡ ንስሐ መግባት፣ ሥጋወ ደሙ ከመቀበል ይልቅ የእነርሱ አድናቂና ካዳሚ እንዲሆን የሚሰቡ ናቸው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቅ ስለ ራሱ ሲናገር ‹እኔ ዝቅ ዝቅ ልል፣ እርሱም ከፍ ከፍ ሊል ይገባል›. ነበር ያለው (ዮሐ. 3፣29)፡፡ ለእነ ቅዱስ ጳውሎስም በልስጥራ እግሩ የሰለለውን ሰው በፈወሰው ጊዜ ሕዝቡ ተደንቆ እንደ አምላክ ሊሠዉላቸው ወድደው ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ግን ‹እንደ እናንተ ሰዎች ነን›. እያለ ለምኖ አስተዋቸው፡፡ ሕዝቡንም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መለሳቸው፤ የእግዚአብሔርም ስም እንዲከብር አደረገ(የሐዋ 14፣8-18)፡፡

በእነዚህና ቤሎችም ምክንያቶች በዘመናችን የተነሡትን ‹አጥማቂ ነን ብለው ማስታወቂያ የሚያስነግሩትን፣ መቁጠሪያና ቅብዐ ቅዱስ የሚያከፋፍሉትን፣ በየሜዳው ሕዝብ ሰብስበው ምትሐት የሚሠሩትን ሰዎች መቀበል አለብን ብዬ አላምንም፡፡ ቤተ ክርስቲያን የጸጋው ግምጃ ቤት ናት፡፡ በጸሎት የሚተጉ፣ በእምነት ሕይወት ያሉ ክርስቲያኖች በየምሕረት አደባባዮች ምሕረትን ያገኛሉ፡፡ በቤተ ሳይዳ መልአኩ ውኃውን ይባርከው እንደነበር ሁሉ የጠበል ቦታዎችን ራሱ እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ባርኳቸዋል፡፡ የተለየ አጥማቂ አያስፈልገቸውም፡፡ የክህነት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው እንጂ፡፡ ደግሞም ሁሉም ሕመም መዳን የለበትም፡፡ ደዌ ዘእሴት(ለበጎ የሚሰጥ ሕመም) አለ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ የብዙዎችን ሰይጣን እያስወጣ እርሱን ግን የሚጎስመው ሰይጣን ነበረው፡፡ ጌታን ሲለምንም ‹‹ተወው›› ነው የተባለው(2ኛቆሮ. 12፣ 7)፡፡ የዛሬ አጥማቂ ነን ባዮች ግን ሁሉም ሕመም ይድናል ይላሉ፡፡ ለቅዱስ ጳውሎስ ያልተቻለ ተቻላቸውን? ከሐዋርያት አንዱ የነገረው ያዕቆብ እግረ በሽተኛ ነበር(ዜና ሐዋርያት፣ በእንተ ያዕቆብ ሐዋርያ)፤ እርሱ ግን ብዙዎችን ይፈውስ ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር ምሕረት አገኘን የምንለውም ስንፈወስ ብቻ መሆን የለበትም፤ የምንታገሥበት ዐቅም ስናገኝም ጭምር እንጂ፡፡ ልመናችንም ለፈውስ ብቻ ሳይሆን ለመታገሥ ዐቅም እንዲሰጠን መሆንም አለበት፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ለመፈውስ የሚችል ቢሆንም ሁሉንም ግን አይፈውስም፡፡ ለበረከት፣ ለተግሣጽ፣ ከከንቱ ውዳሴና ከትዕቢት ለመከላከል የሚፈቅደው ደዌም አለ፡፡ ያዕቆብ ወልደ ይስሐቅ ይህ ተሰጥቶት ነበር(ዘፍ. 32፣ 31)፡፡ ክርስትና በመንፈሳዊ ሕይወት በመኖር፣ በንስሐ መንገድ በመመላለስ፣ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በመሳተፍ እንጂ በድንቅና በተአምራት የሚኖር አይደለም፡፡

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ‹‹ገንዘብ ይሰበስባሉ፣ ገቢ ያስገኛሉ›› ብለው እነዚህን ሐሳውያን እንደሚደግፉ ይታወቃል፡፡ ምእመናንም ‹‹ታድያ አቡነ እገሌ ለምን ፈቀዱ›› ይላሉ፡፡ እኛ ግን መሠረት ማድረግ ያለብን የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን፣ታሪከ ቤተ ክርስቲያንን፣ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ነው፡፡ ማንም ከዚህ የወጣ ቢኖር ትምህርቱን ለመቀበል አንገደድም፡፡ ታላቅነት በእምነት እንጂ በሥልጣን አይገኝምና፡፡ ታላቁ አባት ዲዮስቆሮስ በ451 ዓም የኬልቄዶን ጉባኤ የልዮንን የሁለት ባሕርይ ትምህርት አልቀበል ሲል የሮም ባለ ሥልጣናት ‹‹እርሱኮ በቅዱስ

ጴጥሮስ መንበር የተቀመጠ የሮም ፖፕ ነውና አለቃህ ነው›› ባሉት ጊዜ ‹‹ሰይጣንም ለቅዱስ ሚካኤል አለቃው ነበረ›› ብሎ ነው የመለሰላቸው፡፡

**ሳንድያጎ፣ ካሊፎርንያ**

**የዘመናችን ‹አጥማቂዎች›፡- የሐሳዊ መሲሕ መንገድ ጠራጊዎች**

**(ክፍል ሁለት)**

**1. ተአምራት ማድረግ የምን ውጤት ነው? ተአምራት ማድረግ** ከሁለት ነገሮች ሊመጣ ይችላል፡፡ ከመንፈሳዊ ብቃትና ከሰይጣን አሠራር፡፡ በክርስትና ሕይወቱ የበረታ ሰው መንፈሳዊ ብቃቱ በሕይወቱ በሚገለጡ ተአምራት ሊታወቅ ይችላል፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን የምናገኛቸው ቅዱሳን በገድል ተቀጥቅጠው፣ ሰማዕትነት ከፍለው፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሚገባ ተጉዘው ዲያብሎስን ድል ሲነሡት በሕይወታቸው ውስጥ ተአምራት ይገለጣሉ፡፡ ይህም ማለት ተአምራት የመንፈሳዊ ብቃት መገለጫ ነው ማለት ነው፡፡ የተአምራት ስጦታ እንዲሁ በድንገት አይገለጥም፡፡ በዚያ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እያደገ፣ እየተገለጠና እየተመሰከረለት በሚመጣ መንፈሳዊ ዕድገት ምክንያት እንጂ፡፡ ለዚህ ሁለት ምሳሌዎች እናንሣ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስና አቡነ ተክለ ሃይማኖት፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ አራት ምዕራፍ ያለው መንፈሳዊ ዕድገቱ በየዘመናቱ ተገልጦልናል፡፡ በፍኖተ ደማስቆ መመለሱ(የሐዋ8)፤ በአንጾኪያ በሱባኤ መኖሩ(የሐዋ13)፣ ለአገልግሎት ተጠርቶ ከበርናባስ ጋር መውጣቱ እና ከአረማውያን፣ ከአይሁድና ከመናፍቃን ጋር ባደረገው ተጋድሎ የምናገኘው በትምህርትና በተአምራት የተገለጠ ሕይወቱ ናቸው፡፡ የቅዱስ ጳውሎስ ሕይወት ቀስ በቀስ እያደገ (ወየሐውር እም ኃይል ውስተ ኃይል እንዲል) የመጣ ነው፡፡

የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ሕይወት በመንፈሳዊ ትምህርት፣ በአካባቢያዊ ተጋድሎ፣ ገዳማትን በመሳለምና በመማር፣ ወንጌልን ለአረማውያን በማስተማር እየተገለጠ የመጣ የማያቋርጥ መንፈሳዊ ዕድገት የነበረው ነው፡፡ ክርስትና ድንገቴ ሊሆን አይችልም፡፡(ለዚህ salvation in a moment የሚለውን የአቡነ ሺኖዳን ትምህርት መስማቱ ወይም ማንበቡ ይጠቅማል) ለዚህ ነው ቅዱሳን የነፍሳቸው ቅድስና በሥጋቸው፣ የሥጋቸው በልብሳቸው፣ የልብሳቸው በጥላቸው፣ በመንበራቸው፣ በነኩት ነገር ሁሉ ተገለጠ የምንለው፡፡

ዛሬ የምናያቸው አጥማቂ ወይም ፈዋሽ የሚባሉ ሰዎች መገለጣቸው ድንገቴ ነው፡፡ የታወቀ፣ እያደገ የመጣና የተመሰከረለት መንፈሳዊ ሕይወት አናገኝባቸውም፡፡ እንዲህ ነበሩ እንዲያ ነበሩ እያሉ ተከታዮቻቸው የሚያወሩላቸም ዛሬ ራሳቸው የነገሯቸውን እንጂ ትናንት በነበረው ሕይወታቸው አያውቋቸው፡፡ እነርሱም ያወቋቸው ማጥመቅ ሲጀምሩ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ የታወቀው በማስተማሩና በተጋድሎው ነው፡፡ ለቅዱስ ጳውሎስ ተአምራት ማድረግ የጸጋው መገለጫ እንጂ አዘውትሮ

የሚያደርገውና ‹‹ኑ ላድርግላችሁ›› ብሎ ሕዝብ የሚሰበስብበት ጉዳይ አይደለም፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ለማስተማር፣ ለመማርና ለገዳማዊ ተጋድሎ በሚሄዱበት ቦታ ሕይወታቸው በተአምራት ተገለጠ እንጂ ክርስትናን በአጥማቂነት አልጀመሩትም፡፡ እስኪ ከዚህ በፊት በመንፈሳዊ ሕይወቱ ወይም በገዳማዊ ተጋድሎው ወይም ሃይማኖትን ለመጠበቅ በከፈለው ዋጋው ወይም ደግሞ በኖላዊ አገልግሎቱ ያወቅነው፣ እግዚአብሔር ሕይወቱን በተአምራት የገለጠለት አንድ ‹የዘመኑ አጥማቂ ወይም ፈዋሽ› አለ? አንዳንዶቹ ከውትድርና እንደመጡ ማጥመቅ ጀመሩ፣ አንዳንዶቹም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል ሞክረው የሚፈልጉትን ዕውቅናና ጥቅም ለማግኘት ሲያቅታቸው ወደ ‹ፈዋሽነት›› መጡ፡፡ አንዳንዶች ‹‹እግዚአብሔር ጸጋ ስለሰጣቸው ነው›› ይላሉ፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋኮ እንደ ጾታ ምን ሳናደርግ የሚሰጥ አይደለም፡፡ ሴትነትና ወንድነት ነው ሰው ለሆነ ሁሉ የተሰጠ፡፡

ከዚህ በተቃራኒው ያለው ተአምራት(ምትሐት) ግን የሰይጣን ሥራ መገለጫ ነው፡፡ ሰይጣን ሕዝቡን ከእውነተኛው መንገድ ለማስቀረት ምትሐትን ይጠቀማል፡፡ ይሄ ምትሐት ደግሞ የእግዚአብሔርን ስም እስከ መጥራት ይደርሳል፡፡

**2. መንፈሳዊ ሕይወት ስንል በአራት መንገድ የሚገለጥ ተጋድሎ ነው፡፡** (1)በዚህ ዓለም በመኖር በተቀደሰ ጋብቻ ጸንቶ፣ በምክረ ካህን ተግቶ፣ በንስሐና በሥጋወደሙ እየኖሩ መንፈሳዊ ግዴታዎችን በመፈጸም (እንደ ቅዱስ ላሊበላና ቅድስት መስቀል ክብራ) (2) በገዳማዊ ሕይወት በመጋደልና በአጽንዖ በኣት(እንደ አቡነ አረጋዊ፣ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ) (3)በክህነት ሕይወት እያገለገሉ ኖላዊ ኄር የሚያሰኝ አገልግሎት በመፈጸም(እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አባት ጸጋ ዘአብ፣ እንደ ግብጹ ፓትርያርክ አቡነ ቄርሎስ))ና (4)እምነትን ለመጠበቅ በሚከፈል ሰማዕትነት(እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ ቅድስት አርሴማ)፡፡

አንድ ሰው በእነዚህ የሕይወት መንገዶች መጓዙን የሚያሳይ፣ እያደገና እየተገለጠ የመጣ ሕይወት ሳይኖረው ድንገት አንድ ቀን ተነሥቶ ሰይጣን አስወጣለሁ፣ ተአምር አደርጋለሁ የሚል ከሆነ ያ ከሰይጣን አሠራር ነው፡፡ በገድለ ተክለ ሃይማኖትና በገድለ አቡነ ፊልጶስ ላይ ማርያን የሚባሉ አስማተኞች በእሳት ውስጥ በመመላለስ፣ የሰዎችን የነገ ሕይወት በመተንበይ፣ አጋንንትን አዝዘው ድንቅ ነገር በማሠራት ይታወቁ ነበር፡፡ እነዚህ ቅዱሳን ግን በተጋድሎና በጸሎት የእነዚህን ሰዎች አሠራር ድል ነሥተውታል፡፡ እነዚያ ማርያን ዛሬ ቢኖሩ ኖሮ ብዙ ተከታይ ይኖራቸው ነበር፡፡ ሲሞን መሠርይ ሮም ከተማ ላይ ሕዝቡን ተሰናብቶ ዐርጓል፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ደርሶ በጸሎት ድል ባያደርገው ኖሮ ብዙ ተከታይ አፍርቶ ነበር፡፡

አንድ ሰው ስመ እግዚአብሔር ስለ ጠራ ብቻ የእግዚአብሔር ነው ማለት አይደለም፡፡ ጌታችን ስለመጨረሻው ቀን ሲናገር ‹›በዚያን ቀን ብዙዎች፡- ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፣ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፣ በስምህስ ተአምራትን አላደረግንምን ይሉኛል፡፡ የዚያን ጊዜም፡- ከቶ አላውቃችሁም፣ እናንተ ዐመፀኞች፣ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ››(ማቴ 8፣22) ብሎ ተናግሯል፡፡ እነዚህ ሰዎች ብዙዎቻችን የማናደርጋቸውን ሦስት ድንቅ ነገሮች አድርገዋል፡፡ (1)ትንቢት መናገር፣ (2)አጋንንት ማውጣትና (3)ተአምር ማድረግ፡፡ ደግሞም እነዚህን የሚያደርጉት በክርስቶስ ስም ነበር፡፡

ለዚህም ነው ‹በስምህ› ያሉት፡፡ ነገር ግን ጌታችን ‹ኑ እናንተ የአባቴ ብሩካን› አላላቸውም፡፡ ሦስት አስደንጋጭ መልሶች ለሦስቱ ክህደቶቻቸው ተሰጥቷቸዋል፡፡ (1)ከቶ አላውቃችሁም፣(2) እናንተ ዐመፀኞች፣ (3)ከእኔ ራቁ፡፡

ልክ ዛሬ ሽንጣችን ገትረን እንደምንከራከርላቸው ‹አጥማቂ ነን ባዮች› ትንቢት እየተናገሩ፣ ተአምራት እያደረጉ፣ አጋንንት እያወጡ? ለምን በጌታ ዘንድ ግን ዐመፀኞች ተባሉ፣ ለምን አላውቃችሁም ተባሉ፣ ለምንስ ከእኔ ራቁ ተባሉ፡፡ መልሱ ግልጥ ነው፡፡ ይኼ በምትሐት የመጣ የማስመሰያ ተአምር እንጂ በመንፈሳዊ ተጋድሎ ምክንያት የተገለጠ ጸጋ አይደለም፡፡ ስለዚህም ሕዝብ ያውቃቸዋል እንጂ ክርስቶስ አያውቃቸውም፡፡

**3. ታድያ እነዚህ ሰዎችኮ ፈወስን ይላሉ፤ አጋንንትም ሲናገሩላቸው እንሰማለን፣ በካሴትም ተሸጦ ገዝተን ሰይጣንን ሰምተናል፤ተፈወስን የሚሉም አሉ፡፡ እንዴት ነው?** የእግዚአብሔር ጸጋ በተጋድሎ የምትገኝ ናት፡፡ ‹‹እንበለ መከራ ኢይትረከብ ጸጋ›› እንዲል፡፡ አንድ ሰው የተለየ መንፈሳዊ ሕይወት፣ የተለየም ተጋድሎ ከሌለው በቀር ዝም ብሎ ከሁሉ የተለየ ጸጋ አያገኝም፡፡ ለዚህም ነበር ቅዱስ ጳውሎስ በፍኖተ ደማስቆ ጌታ ከተገለጠለት በኋላ አንዴ ተገልጦልኛልና እፈውሳለሁ ብሎ ያልተነሣው፡፡ በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ጾም፣ ጸሎትና ቅዳሴ ያለበት ሱባኤ ይዞ ነበር(የሐዋ13)፡፡ ከዚህ በኋላ የምናየው የቅዱስ ጳውሎስ ሕይወት የዚህ ሕይወቱ መገለጫ ነው፡፡ ያም አልበቃው ብሎ ‹‹ራሴን እየጎሰምኩ አስገዛዋለሁ›› በማለት እንደነገረን በገድል ላይ ነበር፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የታወቀ ነበር፡፡ በኋላም በተጋድሎው ጸና፤ እርሱ በደም ለመሰከረለት ቅዱስ ጊዮርጊስ እግዚአብሔር በተአምራት ቅድስናውን መሰከረለት፡፡

አሁን የምናያቸው ‹‹እናጠምቃለን› ባዮች ግን ሥራቸው ማጥመቅ ብቻ ነው፡፡ እዚህ ገዳም በእንዲህ ዓይነት ሕይወት ነበሩ ብሎ የሚመሰክርላቸው ገዳም፣ እዚህ አጥቢያ በክህነት እያገለገሉ መንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲህ ነበረ፣ ምእመናንን ለንስሐና ለሥጋ ወደሙ ሲያበቁ ነበረ፤ በመንፈሳዊ ሕይወት የበረቱ ብዙ ክርስቲያኖችን በመንፈሳዊ አገልግሎታቸው አፍርተው ነበረ ብሎ የሚመሰክርላቸው አጥቢያ፣ ወይም ሰማዕትነታቸው እንዲህ ሆኖ ከከሐድያንና ከመናፍቃን ጋር ተገልጦ ነበር የሚል የለም፡፡ በአንጾኪያ ሱባኤ ላይ አናውቃቸውም፣ ተአምራት ግን ያደርጋሉ፣ በጽላልሽ ሲማሩና ሲጋደሉ አናውቃቸውም፣ ፈውስ ሰጠን ይላሉ፡፡ በደብረ ጎልና በደብረ ሐይቅ አናውቃቸውም ተአምር አደረግን ግን ይላሉ፡፡ ይሄ ከሰይጣን ብቻ የሚመጣ ነው፡፡

**4. ቅዱስ ጳውሎስ የሐሳዊ መሲሕን አመጣጥ ባስረዳበት ዐንቀጽ ‹‹የእርሱ መምጣት በተአምራት፣ ሁሉና በምልክቶች፣ በሐሰተኞች ድንቆችም በዐመጽ መታለል እንደ ሰይጣን አሠራር ነው›› ብሎ ነበር(2ኛ ተሰ. 2፣9)፡፡** ቅዱስ ጳውሎስ ለምን ‹እንደ ሰይጣን አሠራር ነው›› አለ? ሰይጣን ሰውን ለማታለል ከፊል እውነት ስለሚያቀርብ፡፡ እኔ አላውቃችህም የተባሉት ተአምር አድራጊዎችም ትልቁ ችግራቸው ሕይወታቸው የዓለም ንግግራቸው የክርስትና ስለነበር ነው፡፡ ባለፈው የጠቀስናቸው የአስቄዋ ልጆች በንግግራቸው ‹‹ጳውሎስ በሚያስተምረው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም›› እያሉ ነበር አጋንንትን ሊያወጡ የሞከሩት(የሐዋ. 19፣14)፡፡ አሠራራቸው ለጥቅም ቢሆንም የተናገሩት ግን ስሕተት

አልነበረውም፡፡ ጳውሎስ የሚሰብከው ክርስቶስ ነው፡፡ በክርስቶስም ስም አጋንንት ይወጣሉ፡፡ይህንን ነው ቅዱስ ጳውሎስ ‹የሰይጣን አሠራር› ያለው፡፡ የሰይጣን አሠራር ማለት አንድን ስሕተት ትክክል እንዲመስል አድርጎ መሥራት ማለት ነው፡፡

ይህ እንዲሆን ለምን እግዚአብሔር ፈቀደ? ቅዱስ ጳውሎስ መልሱን ይሰጠናል፡፡ ‹‹ነገር ግን በዐመጽ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል(2ኛተሰ. 2፣12)፡፡ ንስሐ ላለመግባት፣ የዐመጽን ሥራ ላለመተው፣ ወደ ኦርቶዶክሳዊት ሕይወት ላለመመለስ ባመጽን ቁጥር ሐሳውያን መሲሐውያን መላካቸው የማይቀር ነው፡፡ ‹‹ሐሰትን ያምኑ ዘንድ›› እንዳለውም እኛም ሐሰቱን ማመናችን አይቀሬ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ለስሕተት አሠራር የሚጋለጡት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያልኖሩ፣ መንፈሳዊ ዕውቀት የጎደላቸው፣ ነገሮችን ሁሉ ከጥቅም ጋር የሚያገናኙና መንፈሳዊ ሕይወትን ያልተገነዘቡ ናቸው፡፡ መንፈሳዊ ሕይወት ደቀ መዝሙርነት እንጂ ተከታይነት አይደለም፡፡

ነቢዩ ሆሴዕ ‹ሕዝቤ ዕውቀት በማጣት ጠፋ››(ሆሴዕ 4፣6) እንዳለው የቤተ ክርስቲያንን ዶግማና ቀኖና፣ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ፣ ብሎም ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚገባ አለማወቃችን ከመንፈሳዊ ዕድገትና ለውጥ ይልቅ ተአምራትና ድንቅ ፈላጊ እንድንሆን እያደረገን ነው፡፡ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያችን ‹‹ራእይ እናያለን፣ አጋንንት እናስወጣለን፣ ተአምር እናደርጋለን የሚሉ መሰል ባሕታውያን ተነሥተው ነበር፡፡ ብዙ ሺ ሕዝብ ተከተላቸው፡፡ አብሯቸው በየገዳማቱ ዞረ፤ አሜሪካ ድረስ መጥተው ሲያጠምቁና ሰይጣን አወጣን ሲሉ ኖሩ፡፡ መጨረሻቸው ግን ለሁላችንም ግልጥ ነበር፡፡ ለራሳቸውም፣ ለእኛም ለቤተ ክርስቲያንም ሳይሆኑ ቀረ፡፡ የተከተላቸውም ሰው፣ ሰይጣን አስወጡልኝ ሲል የነበረውም ሰው ተመልሶ ወደ ጥንት ሕይወቱ ገባ፡፡ ዛሬም ይሄው ነው የተደገመው፡፡ ሞኝ ማለት በተመሳሳይ መንገድ እየተጓዘ የተለየ ውጤት የሚጠብቅ ነው እንዲሉ፡፡

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማስተማር፣ መቀደስ፣ ገዳማዊ ሕይወት፣ እንግዶችን መቀበል፣ ከመናፍቃንና ከሐድያን ጋር መጋደል የዘወትር ሕይወታቸው የነበሩ ቅዱሳን ነበሩ፣ አሉም፡፡ እያጠመቁ ሰይጣን ማስወጣት ብቻ ሥራቸው የነበሩ ቅዱሳን ግን የሉም፡፡ ይኼ የደቂቀ አስቴዋ ጠባይ ነው፡፡ ወይም በማጥመቅና ሰይጣን በማባረር ብቻ የሚታወቁ ቅዱሳን አልነበሩም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ‹‹ስለሚያስተምሩ ነው የምንከተላቸው›› ብለዋል፡፡ አሁን ከዛሬ ጀምሮ ማጥመቅና ሰይጣን ማስወጣት አቁመናል ብለው ትምህርት ብቻ ቢያስተምሩ እውነት ትሄዳላችሁ? ቅዳሴ አስቀርቶ በየሜዳው ፈውስ ፍለጋ የሚያንጋጋን የትምህርት ፍቅር ነው?

እንዲያውም በቤተ ክርስቲያን ታሪክም ሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ኪዳን የተሰጣቸው የጠበል ቦታዎች ነበሩ እንጂ የታወቁ አጥማቂዎች አልነበሩም፡፡ በአካባቢው ያሉ ካህናት በቃል ኪዳን የጠበል ቦታዎች ተመድበው ያጠምቃሉ ወይም በአጥቢያቸው ለሚገኙ ሕሙማን ጠበል ይረጫሉ፡፡ ጌታችን ወደ ሰሊሆም መጠመቂያ የላከውን ሰው ወደ መጠመቂያው እንጂ ‹‹እገሌ ወደሚባል አጥማቂ ሂድ›› አላለውም(ዮሐ.9፣6)፡፡ በቤተ ሳይዳም የእግዚአብሔር ምሕረት በመልአኩ በኩል ሲወርድ ሕሙማን ይፈወሱ ነበር እንጂ ‹እገሌ የሚባል ሰው ሲያጠምቅ ተገኘ› አልተባለም(ዮሐ 5)፡፡ ነቢዩ ኤልሳዕም ከሶርያ የመጣውን

ንዕማንን ‹ሂድና በዮርዳኖስ ታጠብ(ተጠመቅ)› አለው እንጂ ‹እገሌ ያጥምቅህ›. አላለውም(2ኛ ነገሥት 5፣ 10)፡፡ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአቡነ ሐራ ድንግል፣ በቅዱስ ላሊበላ፣ በዋንዛዬ፣ በእንጦጦ ኪዳነ ምሕረት፣ በሸንኮራ ዮሐንስ፣ በጻድቃኔ ማርያም ታሪክ በጠበሉ እግዚአብሔር የሠራው ሥራ ተገልጧል እንጂ የአንድ የተለየ አጥማቂ ሥራ የለበትም፡፡ ታድያ ዛሬ ከየት አመጣነው? ከጠበሉ ወደ አጥማቂው መዞር፡፡

**5. እጅግ አስገራሚው ነገር ደግሞ ‹ሰይጣን በመቁጠሪያ ሲደበደብ ይወጣል› የሚለው አስተምህሮ ነው፡፡** ይኼ አስተምህሮ ሁለት ስሕተት አለበት፡፡ የመጀመሪያው በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ለጸሎት ማስታወሻና ማንቂያነት የምንጠቀምበትን መቁጠሪያ ከሥርዓቱ ውጭ በመውሰድ ነገ የእነዚህ ሰዎች የስሕተት አሠራር እንደ ቀደምቶቻቸው ተጋልጦ ሲወድቁ ሕዝቡን መቁጠሪያ እንዲንቅ ያደርገዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች በጾምና በጸሎት፣ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንና በመንፈሳዊ ሕይወት ሳይሆን ሰይጣን በጉልበት ይወጣል ብለው እንዲያስቡ ያደርጋል፡፡

መቁጠሪያ አገልግሎቱ ለጸሎት ነው፡፡ በተለይም በየሰዓቱ እንዲያስታኩቱ የሚታዘዙት መነኮሳት ለጸሎት ማስታኮቻ ይጠቀሙበታል፡፡ ምእመናን ባለ መቁጠሪያ የሆኑት አሁን በኛ ዘመን ነው፡፡ አንድ ቅዱስ አባት ሲጸልይበት የኖረው መቁጠሪያ በረከቱ አደረበት ቢባል መልካም፡፡ የቅዱስ ጳውሎስ በረከት በልብሱ ላይ እንዳደረው፡፡ ከዚያ ውጭ ግን በገፍ መቁጠሪያ ገዝቶ እያከፋፈለ በዚህ መቁጠሪያ ራስን በመግረፍ ሰይጣን ይወጣል ብሎ ያስተማረ፣ ሰይጣንንም በመቁጠሪያ ሲያወጣ የኖረ አንድም ቅዱስ የለም፡፡ እስኪ አምጡ? በየትኛው ገድል አገኛችሁት? ከየትኛው ቅዱስ ተማራችሁት? መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን የሚወጣው በጾምና ጸሎት መሆኑን ያስተምረናል(ማቴ17፣21)፡፡ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቅዱሳን የባረኩት መቋሚያቸው፣ አጽፋቸው፣ ጸበላቸው ድውይ ሲፈውስ እንደነበር ይተርክልናል፡፡ ለመሆኑ የትኛው የዘመኑ አጥማቂ ነው በገድል ተቀጥቅጦ በረከቱን ለመቁጠሪያ ያተረፈው?፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዛሙርቱ ‹ከእኔ የተማራችሁትን፣ የተቀበላችሁትን፣ የሰማችሁትን፣ ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ››(ፊልጵ. 4፣9)ብሎናል፡፡ እኛ ከማንኛው ሐዋርያ፣ ከየትኛውስ ቅዱስ ነው በመቁጠሪያ መደብደብ የተማርነው፡፡

**6. በሰይጣን መፈተንና በሰይጣን መያዝ የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡** አንድ ሰው በክርስትና ሕይወት ከኖረ፣ የጾምና የጸሎት ሕይወት ካለው፣ በቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት(በተለይ ምሥጢረ ንስሐና ቁርባን) ተሳታፊ ከሆነ ሰይጣን በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፡፡ ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ሰው አይፈተንም ማለት አይደለም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በልብሱ እራፊ አጋንንትን እያወጣ እርሱ ግን ከዲያብሎ በሚደርስበት ጉስማት ይሰቃይ ነበር(2ኛ ቆሮ. 12፣8)፡፡ ይህም በዲያብሎስ መፈተን ነው፡፡ ኢዮብ በዲያብሎስ ተፈትኗል፡፡ በዲያብሎስ ቁጥጥር ሥር ግን አልነበረም፡፡ ‹‹ኢዮብ እንደታገሠ ጌታም እንደፈጸመለት አይታችኋል›› በማለት ቅዱስ ያዕቆብ የገለጠውም ይኼንኑ ነው(ያዕ.5፣10)፡፡ አሁን ግን ሁሉም በሰይጣን ተይዟል፣ ተተብትቧል፣ እንዲያውም ገና በማለዳ ነው የተያዘው እየተባለ ነው፡፡ በሰይጣን ይሄ ሁሉ ሰው ከተያዘ ያውም በቁርኝት፣ ክርስትና ወዴት አለ? የተጠመቅነው ጥምቀት፣ የተቀበልነውስ ቁርባን ሥራ መሥራት አቆመን? እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ከአጥማቂዎች በፊት ቤተ ክርስቲያን አልነበረቺም? ወይም

ስታደርገው የነበረቺው ሁሉ ጥፋት ነበር ማለት ነው? ሰው ሊፈተን ይችላል፡፡ በዲያብሎስ ቁርኝት መልሶ ሊያዝ ግን አይችልም፡፡ ክርስትናውን ፈጽሞ ትቶ ‹እክህደከ ሰይጣን›› ባለበት ልቡ ‹‹እክህደከ ክርስቶስ›› ካላለ በቀር፡፡ ምእመናን የበረከት ጥምቀት የሚያስፈልጋቸው በመንፈሳዊ ተጋድሏቸው ውስጥ የሚደርስባቸውን ፈተና ለመዋጋት አንዱ የመውጊያ መንገድ ስለሆነ እንጂ ያለ መንፈሳዊ ተጋድሎ ከሰይጣን ነጻ ለመሆን አይደለም፡፡

**7.በሰው ላይ በሁለት መልኩ ተአምራት ይታያል**፡፡ አንዱ የእግዚአብሔርን ክብር ለመግለጥ፡፡ ይኼ በሰው ላይ ብቻ ሳይሆን በእንስሳትም፣ በዕጽዋትም፣ በግኡዛን ነገሮችም ላይ ይገለጣል፡፡ የኤርትራ ባሕር የተከፈለው፣፡ በካይሮ አጠገብ የነበረው ተራራ(አል ሙከተም) በቅዱስ ስምዖን ጸሎት የተነሣው፣ የቢታንያ ድንጋዮች የተናገሩት፣ በእነርሱ ቅድስና አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ክብር ይገለጥ ዘንድ ነው እንጂ፡፡ በሰዎችም ላይ እንዲሁ ሆኖ ያውቃል፡፡ ቀያፋ ስለ ጌታችን ሞት ትንቢት ተናግሯል(ዮሐ. 12፣ 49)፡፡ ይህ ግን የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ ላይ ተገለጠ እንጂ ከቀያፋ ሕይወት ጋር አይያያዝም፡፡ ቀያፋ እንደካደ ቀርቷል፡፡

ያለ መንፈሳዊ ሕይወት በሰው ላይ የሚገለጥ ተአምር ሰውዬውን አይጠቅመውም፡፡ የእግዚአብሔርን ክብር ግን ይገልጣል፡፡ ልክ የቢታንያ ድንጋዮች በመዘመራቸው እንዳልተጠቀሙት፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ክብር እንደገለጡት፡፡ ከዚህ ዓይነት ሰው የሚወጣ ሰይጣንም(ያውም ከወጣ) ተመልሶ ይገባል፡፡ ያውም ከእርሱ የከፉ ሰባት አጋንንትን ይዞ(ሉቃ. 11፣24-27)፡፡ በገድለ ተክለ ሃይማኖት ላይ አባታችን በአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም እያሉ፣ አንድ በሽተኛ መጣ፡፡ የገዳሙ አባቶችም ሰይጣንን አስወጡት፡፡ ሕመምተኛውም ደኅና ሆኖ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡ ሰይጣን ግን መንገድ ላይ ጠብቆ ተመለሰበት፡፡ ልጁም ከብዙ ጊዜ በኋላ እንደገና መጣ፡፡ አሁንም ሰይጣኑ ወጥቶ መልሶ ገባ፡፡ ይህንን ምሥጢር የተረዱት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ብቻ ነበሩ፡፡ ዛሬም ወጣን የሚሉት አጋንንት ለጊዜው ሰውን አስደስተው ተመልሰው ይገባሉ፡፡ አጥማቂዎቹም አልበቁም፣ ደግሞም ተከታይ እንጂ ክርስቲያን አላፈሩምና፡፡ ለዚህም ነው በአንዱ ‹አጥማቂ› ዘመን ሰይጣን የወጣላቸው ሰዎች እንደገና ሌላ ‹አጥማቂ› ሲመጣ መልሰው የሚለፈልፉት፡፡ ሁሉም በመተታቸው ስለሚያስለፈልፉ፡፡

**8. ሌላው አሳዛኝ ነገር ምሥጢረ ቀንዲል የነዚህ ‹አጥማቂ ነን ባዮች› መጨዋቻ መሆኑ ነው**፡፡ በመጽሐፈ ምሥጢረ ቀንዲል እንደተገለጠው ምሥጢረ ቀንዲል የራሱ ጸሎት አለው፡፡ በአንድ ካህን ብቻም አይፈጸምም፡፡ ከዘይቱ ጋር የሚበራው መብራትም የሚበራበት የራሱ ሥርዓትና ጊዜ አለው፡ ሰባቱ መብራቶች በሰባቱ ጸሎቶች ጊዜ ይበራሉ፡፡ አሁን የምናየው ግን ሰዎች ይመጣሉ፣ ምሥጢረ ቀንዲል አይደገምም፣ የሚበራ መብራት የለም፣ የሚደርስ ኪዳን የለም፤ እንዲሁ ፣አጥማቂዎቹ› እየተነሡ ዘይት ያፈሳሉ፡፡ ይኼ ከማን ያገኘነው ሥርዓት ነው? ምሥጢረ ቀንዲል ያለ ምሥጢረ ቀንዲል ጸሎትና ሥርዓት ሲፈጸም ያየነውስ የት ነው? ከምሥጢረ ቀንዲል በፊትም የሚቀድም ሥርዓት አለ፡፡ መጽሐፈ ምሥጢረ ቀንዲል በዝርዝር አስቀምጦታል፡፡ አንብቡት፡፡ ወይም የሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየን(በረከታቸው ይደርብንና) ‹**ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን**›› የተሰኘውን መጽሐፍ አንብቡ፡፡ አለበለዚያም ደግሞ ብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ ያዘጋጁትን ‹**ምሥጢራ ቤተ ክርስቲያን**› የተሰኘውን

ማስተማሪያም ተመልከቱ፡፡ አሁን የሚከናወነውን ‹የአጥማቂዎች› የዘይት ማፍሰስና ማጠጣት ሥርዓት የሚመስል ነገር ፈጽሞ በቤተ ክርስቲያን አልነበረም፡ ይህንን ሕገ ወጥ ሥራ የሚሠሩ አጥማቂዎች ናቸው እንግዲህ ‹‹ድሮ እዚህ ተምረናል፣ ሰርተፊኬት ወስደናል›› እያሉ የሚያታልሉት፡፡ ታድያ የታለ ትምህርቱ በተግባር የተገለጠው?

**9. ክርስትና ስለ ክርስቶስና በክርስቶስም ስለሚገኘው ድኅነት ማመንና መስተማር ነው፡፡** ስለ ቅዱሳንና ስለ ቤተ ክርስቲያን የምንማረውም ቅዱሳን የወይኑ ግንድ ቅርንጫፎች፣ ቤተ ክርስቲያንም የወይኑ እርሻ ስለሆነች ነው፡፡ የዘመኑ አጥማቂ ነን ባዮች ግን ብዙ ጊዜያቸውን የሚያጠፉት ስለ ሰይጣን በማስተማር፣ ሰይጣንን በማስለፍለፍና ሰይጣን ያለውን እየቀዱ በካሴት በመሸጥ ነው፡፡ ምእመናኑም ሰይጣንን ሰምተው ከትዳር አጋሮቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከጎረቤቶቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ይጣላሉ፡፡ መተት፣ ድግምት፣ መድኃኒት ተደርጎብሃል/ሻል እያለ ስለሚነግራቸው፡፡ እስኪ የትኛው ሐዋርያ ወይም ቅዱስ ነው ይህንን ያህል ስለ ሰይጣን የሰበከን? ሰይጣን ገናና ሆኖ፣ ሁሉን የሚቆጣጠር ሆኖ፣ ምእመናንን እንደፈለገ ሃያ ሠላሳ እየሆነ እንደሚሠፍርባቸው ሆኖ እየተሰበከ ነው፡፡ መቼም ሰይጣን በሐዋርያትና በሠለስቱ ምእት፣ በሰማዕታትና በቅዱሳን አበው ያጣውን ቦታ እንደ ዘንድሮ ያገኘበት ዘመን የለም፡፡ ክርስትና ክርስቶስን ወድደን የምንከተለው እንጂ ሰይጣንን ፈርተን የምንከተለው አይደለም፡፡ በአእምሯችን ቦታ ሊኖረው የሚገባውም በመስቀል የተፈጸመልን የማዳን ሥራ እንጂ የሰይጣን ታሪክ፣ አሠራር፣ ትምህርትና ድንቅ ሥራ አይደለም፡፡ አሁን ግን ቦታውን የያዘው ሰይጣን ነው፡፡ ሰው መስማት የሚፈልገው ስለ ሰይጣን ነው፡፡ ስለ ክርስቶስ አይደለም፡፡

**ማጠቃለያ**

በነሐሴ 2007 ዓም በተደረገ አንድ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብቻ 432 የግል አጥማቂዎች እንዳሉ ታውቋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ስማቸው የገነነ አምስት አጥማቂዎች አሉ፡፡ እስካሁን 7 መጻሕፍትንና ወደ 100 የሚጠጉ የሰይጣን ምስክርነቶችን በድምጽና ምስል ለቅቀዋል፡፡ በቅርቡ ዋና ዋና የሥራቸውንና የትምህርታቸውን ሐሳዊ መሲሕነት የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ ይኖራል፡፡ ቸር ያሰንብተን፡፡